**ብራንዲንግ (Branding) ምንድነው ?**

አንድ ድርጅት ሲመሰረት የንግድ ምልክት (Trademark) ሊያስመዘግብ ይችላል። ከዛም ድርጅቱ የሚከውናቸው ተግባራት በተጠቃሚዎቹ ዘንድ የሚኖረው ቦታ በዛ በተሰጠው የንግድ ምልክት ወይም ስያሜ ይገለጻል ማለት ነው። ይህም የድርጅቱ ቃል ጠባቂነት፣ ታማኝነት ለተገልጋዮቹ የሚሰጠው ቦታ፣ ከተገልጋዮቹ ጋር የሚያደርገው ተግባቦት (Communication): በአገልግሎቱ ወይም ምርቱ የሚያሳየው ተመሳሳይነት (consistency) ወዘተ የተመሰረተ ይሆናል።
ይህ ሁለት ነገሮችን ያስታውሰናል ብራንድ መገንባት ሎጎ ወይም ምልክት ከማስመዝገብ የዘለለ ጥልቅ ሃሳብ መሆኑን እና በጊዜ ሂደት በድካም የምንገነባው መሆኑን ነው።

አንድ አንድ ጊዜ ብራንድ ለመገንባት ማስታወቂያ አብዝቶ ማሰራት እንደዋና መንገድ የሚቆጥሩ ድርጅቶች ይገጥሙናል። ማስታወቂያ ማሰራት የብራንድ ሂደቱን የሚያፋጥን አይነተኛ መሳሪያ ነው። ይሁን እና ድርጅቱ ባሰራው ማስታወቂያ ልክ (እንዲሁም በተሻለ) የማይገኝ ከሆነ በመገንባት ላይ ያለውን ብራንድ መሸርሸር (Brand Dilution) ይገጥመዋል። ይህ ደግሞ መልሶ ለመገንባት ቀላል አይሆንም። ስለዚህ ብራንዲግ ከላይ የጠቀስኳቸውን እና ሌሎችንም አሰራር ጥበቦች በአግባቡ መያዝ ሲችል በሂደት የሚገነባ ነገር ነው።

በጥቅሉ ብራንዲንግ አንድ ድርጅት በተጠቃሚዎቹ ላይ የሚፈጥረው በጎ አሻራ (Impression) ነው።

## ብራንድ እና ጥራት?

የንግድ ምልክቶች ሲመዘገቡ የምንሰራው አገልግሎች ወይም የምናመርተው ምርት ምን እንደሆነ አንጠየቅም ወይም በምንሰራው ስራ ላይ ምርመራ ተደርጎ እና ጥራቱ ተረጋግጦ አይሰጠንም። ነገር ግን በጊዜ ሂደት ሰዎች በድርጅቱ አገልግሎት ወይም ምርት ጥራት ላይ እምነታቸው እያደገ ሲመጣ የንግድ ምልክቱ ታዋቂ እየሆነ ይመጣል። ይህ ደግሞ ብራንዲንግ ጥራትን የገልጻል እንዲባል ያስችለዋል።

## ብራንድ እንዴት ይገነባል?

ከላይ የተጠቀሱት እሴቶች እንዳሉ ሆነው ብራንዲንግ ለመገንባት የተጠኑ ሳይንሳዊ መንገዶች አሉት። ለአብነት ያህል የእኛን ድርጅት ከሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች ለየት የሚያደርገው እሴት መኖሩ (Unique value propostion) ፣ተጠቃሚዎቻችንን በአግባቡ መለየታችን (knowing our audinece)እና ያለን ቅርርብ (Engagment and Involvment) እንዲሁም ሌሎች ዘዴዎችን ያካትታል።

*ስለ ብራንዲንግ ወይም ሌላ ጥያቄ ካለዎት ወይም የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ በየሳምንቱ የነጻ ጥያቄ እና መለስ ፕሮግራማችንን ወይም በትሬኒንግ ውስጥ ከተዘረዘሩ ስልጠናዎች መካከል መርጠው ይመዝገቡ። ወይም ኮንታክትን በመንካት ያግኙን!*

© [2025] Shegasab. All Rights Reserved. The unauthorized reproduction, distribution, or transmission of this text is strictly prohibited and subject to legal action under applicable copyright law.